በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ቅድመ ጋብቻ

## ክፍል 1

## ከሥልጣኔ ጋር ተያይዞ ከጋብቻ ውጪ የሚፈጸመውን መሸኮርመምና ማሸኮርመምን በተመለከተና

## የሕይወት አጋራቸውን ለሚፈልጉ
## እግዚአብሔር - መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?


ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ


ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት

ኅዳር ፳፬ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# እግዚአብሔር - መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

ማሽኮርመምና መሽኮርመምን የተመለከተ አጀንዳ በሁሉም ዕድሜ ያሉ ክርስቲያኖችን በእውነትም የሚስብ ወይም የሚማርክ ነው፡፡

ስለዚህ ጉዳይ እግዚአብሔር የሚናገረንን ማወቅ ግን የሁላችንም ኃላፊነት ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በወንድና ሴት መካከል ስለሚኖረው ግኑኝነት የያዘውን ጥቅስ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ትምህርቱን ሕይወት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

ቤተክርስቲያን ሰፊ ጊዜ በመውሰድ የምታስተምርባቸው በርካታ ርዕሶች ቢኖሩም ወጣት ወንዶችና ሴቶች እርስ በርሳቸው ሊያሳዩት የሚገባውን ዝንባሌ በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠንን መመሪያ ገልጦ ከማስተማር አንጻር ግን ብዙ ይጠበቃል፡፡

# የቀጠለ ...

ወንዶች ይኽ ጥቅስ እንደሚያስደስታቸው አልጠራጠርም፡-
#ሚስት ያገኘ በረከትን አገኘ፥ ከእግዚአብሔርም ሞገስን ይቀበላል።; ምሳሌ 18 * 22

ወንዶች ሆይ፡ - *እግዚአብሔር ተከታትለን* አንገላተን* ተጫውተንባቸው ስለምንጥላቸው እጮኞች (Girl Friend) የሰጠን ነጻነት የለም።*

እግዚአብሔር ልጆቹ የሆኑ አማንያን ሁሉ ሌሎችን ተጠቅመውባቸው ሲጥሉ አይወድም። ወጣት ወንዶች ልጃገረዶችን (አካላዊም ሆነ ስሜታዊ) ጉዳት በማድረስ በድለው ሲተዋቸውም ይቀየማል።

መጽሐፍ ቅዱስ በወጣት ወንዶችና ልጃገረዶች መካከል የሚኖረውን ግኑኝነት በተመለከተ የሚገልጸው፡- የረጅሙን ጊዜ ዓላማና መጨረሻም በትዳር የሚጠናቀቀውን ግኑኝነት ድጋፍ አድርጎ ነው።

ይኽን ካላመናችሁ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ራሳችሁን ተመልከቱ።

መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ ዓለም በመለማመድ ላይ የሚገኘውን ከመዝናኛ ጋር ተያይዞ የመጣውን #ላውጣህ - ላውጣሽ;ን በተመለከተ እንድንገፋበት የሚለን የሰጠንም ምንም ነጻነት የለም።

## የመዝናኛው #ላውጣህ - ላውጣሽ; - (Dating) ምንድር ነው?

ለረጅም ጊዜ ዓላማ በሌላቸው መካከል የሚፈጸም ፈቃድ ነው፡፡

#የአእምሮን ስሜታዊ መሻት; ብቻ ለመፈጸም የሚደረግ ነውረኛ ድርጊት ነው፡፡

ለጋብቻ ፍጹም ፍላጎት በማጣት የተነሣ የሚፈጸም ድርጊት ነው፡፡

በአእምሮ ያለውን አካላዊ ፈቃድ መሙላት ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው መግለጫ በሙሉ በዚህ ዓይነት ድርጊት የወደቁ ክርስቲያኖችንም ችግር ጭምር የሚያሳይ ነው፡፡

# የቀጠለ...

እውነተኛ አማኒ አስቀድሞም ለጋብቻ ሕይወት የሚያዘጋጅ ጤናማ ግኑኝነት የሚፈጥረው ከኦርቶዶክሳዊ ጋር ብቻ ነው።

#ከእነርሱም ጋር አትጋባ ሴት ልጅህን ለወንድ ልጁ አትስጥ፥ ሴት ልጁንም ለወንድ ልጅህ አትውሰድ። ; ዘዳግም 7 * 3።

#ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ; 2ኛ ቆሮ 6 * 14።

#ሴት ባልዋ በሕይወት ሳለ የታሰረች ናት፤ ባልዋ ቢሞት ግን በጌታ ይሁን እንጂ

የወደደችውን ልታገባ ነጻነት አላት። 1ኛ ቆሮ 7 * 39

# የቀጠለ...

ካላመኑ ጋርም ሆነ ከኦርቶዶክሳውያን ጋር ከጋብቻ ውጪ የሥጋን ፈቃድ ለመፈጸም መቀጣጠር ከመጽሐፍ የወጣ ነው፤ አልተፈቀደም።፡ ባልገው ኢአማኒ ያገቡ ሰዎች መነሻቸው ከመጽሐፍ የወጣ ኑሮ ነው።

ጥቂቶች የሕይወት አጋሮቻቸው እንደነርሱ በእግዚአብሔር አምነው ቢቀርቡም ብዙዎች ግን ባልተመጣጠነ አኗኗር የተነሣ በመስቃየት ላይ ይገኛሉ።

እግዚአብሔር - ካላመኑ ጋር መጋባት ጥፋት ፤ ኃጢአት ነው ካለ፤ ፈቃድን ለመፈጸም ካላመኑት ጋር መቀጣጠርም ኃጢአት ነው።

እኛም - ትክክለኛ ፈቃዳችንን በታጠረልን ቅጥር ዙሪያ እግዚአብሔር በፈቀደልን መንገድ እንፈጽም እንጂ ፈጽሞ ይህን ነውር አናድርገው።

እግዚአብሔር በዚህ ብቻ ሳይሆን ከጋብቻ አስቀድሞም ሆነ ከጋብቻ በኋላ ያለውንም ግኑኙነት አስመልክቶ የሚነግረን ብዙ አለ።

# ቅድመ ጋብቻ

እግዚአብሔር በቃሉ ያመኑ ሁሉ ያመኑትን ብቻ እንዲያገቡ አዟል። ስለዚህ ማንኛውም ግኑኝነት የሚጀምረው ከኦርቶዶክሳዊነታችን ነው።

*ለወንድና ለሴት የታሰበው ሐሳብ የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው። ይኸውም ፡-*

#ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።; ዘፍጥ 2 * 24

#አለም። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም

አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?; ማቴ 19 * 5

ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ - አበቃ!!! የእግዚአብሔር የጋብቻ ስሌት አንድ አካል መሆን ከፈለግን እንደ መጽሐፉ ቃል አንድ ብቻ መፈለግ አለብን።

የሠለጠነው ዓለም የመፈቃቀድ - የመቀጣጠርና - አብሮ የመዋል ልምድ ጉዳቱ ከብዙዎች ጋር መላመድና ሁሉም ግኑኝነት ወደ ትዳር ሊያደርስ ይችላል ብሎ መገመትና ግኑኝነቱም እንደታሰበው ሳይሆን ቀርቶ ሊፈርስ መቻሉ ነው።

# የቀጠለ…

ያመኑ ሁሉ የዓለምን ልምድና ፍልስፍና አይከተሉም። የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስን መመሪያና የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ብቻ ነው።

ክርስቲያኖች ስሜታዊነት የሌለበትን ዘላቂነት ያለውን የጋብቻ መንገድ ብቻ በመከተል ብቁ እስኪሆኑ ድረስ ይጠባበቃሉ።

በሥጋዊው ወይም የዓለምን ሥልጣኔ በተከተለው መንገድ ሰዎች የሥጋ ፈቃዳቸውን አስቀድመው ይፈጽማሉ፤ አንዳቸውን የሚያበሳጭ ነገር ሲከሰትም ግኑኙነቱ ይበጠሳል። - ዛሬ የፈቺን ቁጥር እንዲበረክት ያደረገው እንዲህ ዓይነት ግኑኙነት ነው።

በዚህ ጨዋታ ውስጥ የሚከሰተው አስገራሚው ቀልድ #ይኽ ካልተሳካ ሌላ እሞክራለሁ; የሚለው ነው።

እግዚአብሔር ቃልኪዳንን - መሐላን መጠበቅ ካልቻልን ፈጽሞ ወደ ግኑንነት እንድንገባ አይፈቅድም።

# የቀጠለ...

#ሰው ለእግዚአብሔር ስእለት ቢሳል፥ ወይም ራሱን በመሐላ ቢያስር፥ ቃሉን አይስበር ከአፉ እንደ ወጣው ሁሉ ያድርግ::; ዘኍ. 30 * 2

#ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህም የወጣ ከክፉው ነው::; ማቴ. 5 * 39

#እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና; ቆላ. 3 * 9

የሥጋ ፈቃዳቸውን ከፈጸሙ በኋላ ሊያፈርሱት - ስንቶች ስለመውደዳቸውና በፍቅር ስለመማረካቸው ቃል ይገባሉ? ይህ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ነው::

# የቀጠለ…

ወጣቶች የሕይወት አጋርን ጉዳይ በርቀት የሚመለከቱ መሆን ይገባቸዋል፡፡

እግዚአብሔር ወደ ወንድ ወይም ወደ ሴት ለተወሰነ ጊዜ ፈቃድን ለመፈጸም ያህል ብቻ መመልከታችንን አያበረታታም፡፡ ክርስቲያንና ለእግዚአብሔርም መኖርን የመረጥን መሆንና፤ ነገርን ሁሉ በአግባቡ በትዕግሥት ከርቀት መመርመር የሚጠበቅብን ለዚህ ነው፡፡

የእግዚአብሔር የሆነ ልብ ከሌለው ጋር በዚህ ዓለም ግኑኝነትን መፍጠርን ስለምን እናስባለን? ለምንስ እንፈልጋለን?

ክርስቲያን የሆኑ ቤተሰቦች ካሉአችሁ የሕይወት አጋር ሊሆኑአችሁ ስለሚችሉት ምክር ወይም አስተያየት መቀበል ትችላላችሁ፡፡

# የቀጠለ...

እስካሁን ድረስ፡-

- የምንመርጠው አጋር ክርስቲያን ኦርቶዶክሳዊ መሆን፡

- ጋብቻም የሚፈጸመው ከዚያ አንዱ (አንዷ) ጋር መሆን እንዳለበት

- በነገር ሁሉ በዝርዝር የእግዚአብሔርን ነገርና መንገድ በማሰብ መወሰን እንዳለብን ተመልክተናል፡፡

# የመጽሐፍ ቅዱስ ምክር

#ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ።; 1ኛ ቆሮ 7 * 9

#ስለ ጻፋችሁልኝስ ነገር፥ ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው።; 1ኛ ቆሮ 7 * 1

#ለቅዱሳን እንደሚገባ ግን ዝሙትና ርኵሰት ሁሉ ወይም መመኘት በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ; ኤፌ 5 * 3

#ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።;1ኛ ቆሮ 6*18

#ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ; 2ኛ ጢሞ 2 * 22

# ማጠቃለያ

ዓለም ባመቻቸችልን መንገድ ምርጫ ብናደርግ ፈቃዳችንንም ብንፈጽም፤ ራሳችንንና የመረጥናቸውን ጎድተን ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረን የሚገባውንም ጤናማ ግኑኝነት እናበላሻለን።

በእግዚአብሔር መንገድ የሕይወት አጋርን መምረጥ የሚገባ ሲሆን እግዚአብሔር የምርጫችንን መመዘኛ አስመልክቶ በትክክል ያስመረልንን የመጽሐፍ ቅዱስን መስመሮች ጥሰን እንዳናልፍ መጠንቀቅ ይኖርብናል።

በመጨረሻ፡-

- *ግኑኝነታችን እስከ ጋብቻ ድረስ አካላዊ እንዳይሆን እንጠንቀቅ።*
- *ጋብቻ የሌለበትን ስሜታዊ መቀራረብ ከመፍጠር እንራቅ።*
- *ልትፈጽሙ የማትችሉትን ቃል ኪዳን አትግቡ።*
- *ካላመኑትም ጋር ሆነ ያለእግዚአብሔር ከሚ[1]ዙ ጋር ኅብረት አናድርግ።*
- *እንደምትጋቡ በትክክል ከምታውቁት በቀር የሕይወትን ግኑኝነት አትጀምሩ።*
- *ከርቀት መርምሩ! - የእግዚአብሔር የሆነ ጠባይ መኖሩን አረጋግጡ። ብዙዎች ደግሞ ማስመሰል እንደሚችሉ አትዘንጉ።*
- *የወላጆቻችሁን ምክርና አስተያየት ችላ አትበሉ።*
- *በማንኛውም ግኑኝነት በእያንዳንዱ ሂደት እግዚአብሔርን አክብሩ።*

ይቀጥላል…

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

ይቆየን።